# ጠበል



ኢየሱስ ክርስቶስ በምራቁ ለውሶ የዕውሩን ዓይኖች ከቀባ በኋላ ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ ዓይንህም ይበራል
ዮሐ. ወንጌል 9፥6-8

ጠበል ማለት ቃሉ የግእዝ ሲሆን ፍቺም አፈር (አቧራ) ማለት ነው። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያናችን ጠበል ብለን የምንጠራው በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ሕሙማን የሚፈወሱበት ተአምራት የሚደረግበት ቅዱስ ውኃ ማለት ነው።

ጠበል ማለት በግእዙ አፈር (አቧራ) ማለት ከሆነ ሕሙማን የሚፈወሱበት ተአምራት የሚደረግበት ቅዱስ ውኃ ስለምን ጠበል ተባለ? የሚል ጥያቄ ቢኖር መልሱ በዮሐንስ ወንጌል 9፥6-8 የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉም እንዲህ ይላል «በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ። ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ፤ በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው። ስለዚህም ሄዶ ታጠበ እያየም መጣ» ይላል። በዚህም ምንባብ ውስጥ እንደምንመለከተው እንደ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ብርሃን ዕውራን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን የተዋሐደ አምላክ ነውና አፈሩን በምራቁ ለውሶ የዕውሩን ዓይኖች ከቀባ በኋላ ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ ዓይንህም ይበራል ስላለው የተባለውን ፈጽሞ ዓይኑ በርቶለታል። ይህ ተአምር የተደረገው ሥጋን የተዋሐደ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምራቁ ለውሶ ጭቃ ባደረገው መሬትና በሰሊሆም መጠመቂያ ከሚገኘው ቅዱስ ውኃ ድብልቅ በመሆኑ ሕሙማን የሚፈወሱበት ቅዱስ ውኃ ጠበል ተብሎ ተጠርቷል።

## ስለጠበል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች

1ኛ. ንእማን የተባለ ከፍተኛ የሶርያ ባለሥልጣን ነበር፡፡ ይህም ሰው ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ እንደበረዶ ነጭ በሆነ ለምፅ የነደደ ነበረ። ከሀገሯ ከእሥራኤል ወደ ሶርያ ተማርካ የሄደችና በዚህ በለምጽ በሽታ በተያዘው ባለሥልጣን ቤት የነበረች አንዲት እሥራኤላዊት ብላቴና በአገሬ በእሥራኤል ምድር ለምፅን የሚፈውሱ ነቢያት አሉ። ንእማን ቢሄድ ይድናል ብላ በተናገረችው መሠረት ለምጻሙ ንእማን ሠራዊት አስከትሎ ወደ እሥራኤል በመሄድ ከነቢዩ ከኤልሳዕ ጋር ተገናኝቶ ስለበሽታው ሲጠይቅ ነቢዩ ኤልሳዕ ለንእማን ከለምፅህ የምትነጻው በዮርዳኖስ ውኃ 7(ሰባት) ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብለህ ታጥበህ ስትወጣ ነው አለው። ንእማንም ሰው በውኃ ከበሽታ እንዴት ይድናል? ብሎ በአሁኑ ዘመን እንደሚጠራጠሩት እንደ አንዳንድ ሰዎች የውኃ ውኃማ በአገሬ በደማስቆ የሚገኙት ወንዞች አባናና ፋርፋ ከእሥራኤል ወንዞች አይሻሉምን? በማለት በከፍተኛ ብስጭት ወደ አገሩ ሲመለስ የራሱ ተከታዮች የከበደ ነገር አልጠየቀህም እምነህ በውኃ ታጠብ ነው ያለህ ለምን አትታጠብም አሉት። የተከታዮችንም ቃል በመስማት ተመልሶ በእምነት በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብሎ ሲወጣ ከለምፁ ተፈውሷል። 2ነገሥ.5፥1-15። በተለይም ቁጥር አሥራ አራትን ይመልከቱ።

2ኛ. በኢየሩሳሌም ውስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ እንደነበረችና በእርሷም ውስጥ ያለውን ውኃ የእግዚአብሔር መልአክ እየባረከው በዚህ ቅዱስ ውኃ በሽተኞች፥ እውሮች፥ አንካሶችም ሰውነታቸውም የሰለለ ሁሉ ይድኑ እንደነበረ እንረዳለን። ዮሐ.5፥2-5። በዚህ በተጠቀሰው ምዕራፍና ቁጥር ውስጥ 38 ዓመት ሙሉ በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ ተይዞ የኖረ አንድ በሽተኛ ሰው እንደነበረና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን ሰው በዚያው ቦታ አግኝቶት ልትድን ትወዳለህን? ብሎ በጠየቀው ጊዜ መልአኩ ውኃውን ሲባርከው ውኃ ውም ሲንቀሳቀስ ወደ ውኃው የሚያስገባኝ ዘመድ በማጣቱ እንጂ እኔማ እድንን ዘንድ እወድ ነበር ብሎ ስለመለሰለት እንደ ኤልሳዕ በውኃ ታጠብ ሳይል በቃሉ ብቻ ተነሣ አልጋህንም ተሸክመህ ሂድ በማለት ፈውሶታል።

ይህንን መንሥኤ በማድረግ በሐዲስ ኪዳን በቃሉ ብቻ እንጂ ጠበል የተባለ ውኃ አያስፈልግም የሚሉ አሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ጠበሉ የሚያስገባው ዘመድ ያጣውን ይህን ሰው ወደ ውኃው በማስገባትና በውኃው በመፈወስ ፈንታ በቃሉ ብቻ የፈወሰው በሐዲስ ኪዳን ጠበል የተባለ ቅዱስ ውኃ አያስፈልግም ለማለት አይደለም። እኛ የሰው ልጆች በምንቸገርበት ጊዜ ወደ ጠበል የሚወስደን ዘመድ ብናጣ በአንቦት አልጋ ላይ ሆነን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ማረን ብለን ብንጸልይ ምሕረቱ መለኮቱ በሁሉም ቦታ የሚገኝ አምላክ በቃሉ ብቻ የሚፈውሰን መሆኑን ሊያረጋግጥልን ስለ ፈለገ ብቻ ነው። ይልቁንም የጠበሉ ባለቤት አምላካችን ራሱ በዚያ በመገኘቱና ሰዚህ ሰው ወደጠበሉ መሄድ ስላላስፈለገው ነው።

3ኛ. በሐዲስ ኪዳን ጠበልን ባርኮ እንደሰጠን ተጨማሪ መረጃ «ሲያልፍም (አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ፤ ደቀ መዛሙርቱም መምህር ሆይ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ? ብለው ጠየቁት።

ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ
መለሰ፡፡ የእግዚአብሔር ሥራ በእ
እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይ
ወላጆቹ ኃጢአት አልሰሩም። በር
ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባ
ማንም ሊሰራ የማይችልባት ሌሊ
ትመጣለች። በዓለም ሳለሁ የዓ
ብርሃን ነኝ ይህን ብሎ ወደ መ
እንትፍ አለ፤ በምራቁም ጭ
አድርጎ በጭቃው የዕውሩን ዓይ
ቀባና ሂድና በሰሊሆም መጠመ
ታጠብ አለው፤ ስለዚህ ሄዶ ታ
እያየም መጣ» ይላል ዮሐ.9፥1-
በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠ
ሁሉን ቻይ አምላክ መድኃኒ ዓ
ክርስቶስ ይህን ዓይን የሌለውን
በሰሊሆም መጠመቂያ ታጥበህ
ዓይንህ ይበራል ብሎትና ሰውየው
እንደታዘዘው ተጠምቆ ዓይኑ
ለት፡ በቃሉ ብቻ ዓይኑን ማብ
አቅቶት ሳይሆን በበሉይ ኪ
ሕሙማን ይፈወሱበት ተአም
ይደረግበት የነበረው ቅዱስ
(ጠበል) በሐዲስ ኪዳንም የተባረ
ፈቃድ የሰጠን ፀጋ መሆኑን ለ
ረዳት ነው።

ይህ መረጃ በሚቀርብበት
መልክም መቀበሉንስ እንቀበለው
ማን ጌታችን ኢየሱስ ክርስ
በዮሐ.14፥14 ሁሉን ነገር በ
ለምኑ ይልና በተጨማሪ
በሐዋ.4፥12 ላይ «ከሰማይ በ
ከምድር በላይ መዳንም በሌላ በማ
የለም እንድንበት ዘንድ የሚገ
ለሰዎች የተሰጠ ስም ሌላ የለ
ይላል። ስለዚህ ጠበሎች ሁሉ በ
በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠ
ሲኖርባቸውና አዳኙም እርሱ
መሆን ሲገባው ለምን የድንግል
ያም ጠበል፥ የሚካኤል፥ የገ
ኤል፥ የጊዮርጊስ፥ የገብረ መ
ቅዱስ ወዘተ...ጠበል ተባለ? የሚ
አሉ።

መልሱ አጭር ነው። ይኸው
በጠበሉ ቅዱሳኑ እንዲታሰቡ

ነው። በኢሳይያስ 56፥4-6። ባለው ምንባብ ውስጥ፥ «ደስ የሚያሰኘኝን ነገር ለመረጡ ቃል ኪዳኔንም ለጠበቁ ጃንደረቦች ከሴቶች ልጆችና ከወንዶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ በቤቴና በቅጥሬ መታሰቢያቸውን አደርጋለሁ፥ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ» ባለው ቃል መሠረት ነው። እዚህ ላይ ጃንደረባ የሚለው ቃል በማቴዎስ 19፥12። ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን ጃንደረቦች ያደረጉ አሉ። በማለት የዚህን ዓለም ፍትወትን፥ ፍቅሩን ሁሉ ትተው መስቀሉን ተሸክመው በብቸኝነት ራሳቸውን ያሳለፉትን ቅዱሳኑን መሆኑን ያረጋግጣል። በተጨማሪም «የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ነው» ይላል መዝ.፥111፥7። መታሰቢያቸውም ለበረከት እንደሆነ ለማረጋገጥ «የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው» ይላል ምሳ.10፥7። በዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ መሠረት በጠበሉ ቅዱሳኑ መጠራታቸው መታሰቢያቸው እንዲሆን ነው። መታሰቢያነት ብቻም ሳይሆን በረከትነትም አለው ብለን እናምናለን እንጂ፤ ጠበሉን የፈጠረው መድኀኒ ዓለም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑና በጠበሉም አድሮ ሕሙማንን የሚፈውሰውና ተአምራትንም የሚያደርገው ሁሉን ቻይ የሆነው የአምላካችን የእግዚአብሔር ኃይል መሆኑ ጠፍቶን አይደለም። በጠበል ታጥበን እንድንፈወስ የሆነው በሚታዩ በሚጨበጡ ቅዱሳት ምልክቶች የማይታየውን የማይጨበጠውን አጋንንትን በማባረር፥ ሕሙማንን የመፈወስ ተአምራትን የማድረግ ረቂቅ ኃይሉን እንዲያስተላልፍባቸው ስለፈቀደ ነው። ለምሳሌ ያህል፦

1. የኤርትራ ባህር የመክፈል ኃይሉን በሙሴ በትር ዘጸ.14፥15-17።

2. ሙት የማስነሳት ኃይሉን በዐፅመ ኤልሳዕ.2ነገ.13፥20።

3. ድውያትን የመፈወስ ኃይሉን በቅዱስ ዘይት፤ ማር.6፥14፤ ያዕ.5፥14።

4. አጋንንትን የማባረር ኃይሉን ቅዱስ ጳውሎስ ለብሶት በነበረው ልብስ የሐዋ.19፥11።

እንዳስተላለፈ ሁሉ በዚህ ጠበል ተብሎ በተጠራው በቅዱሱ ውኃም እስከአሁን ድረስ ወደፊትም ሕሙማንን የመፈወስ ታአምራትን የማድረግ ረቂቅ ኃይሉን እያስተላለፈልን እየተፈወስን እንገኛለን። ወደፊትም እንፈወስበታለን። ለዚህ ምሳሌ የአዲስ አበባ ኪዳነ ምሕረትን፥ ቀ/ሃይማኖትን፥ ገ/መንፈስ ቅዱስን፥ ዑራኤልን፥ የሚጣቅ አማኑኤልን፥ የሰብታ ኢየሱስን ጠበል መጥቀስ በቂ ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ኃይሉን በገለጠባቸው ማደሪያዎቹ በደረጋቸው የጠበል ቦታዎች ሰዎች ከደዌ ሥጋ ተፈውሰው ከሥቃይ አምልጠው በሰው ፊት እንደሰው ለመኖር በቅተዋል። ንዕማን የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ኤልሳዕ የነገረውን ሰምቶ በሃይማኖት ወደ ዮርዳኖስ ወረደ፤ ተጠመቀም፤ በሰዎች ፊት ያሳፍረው ከነበረው ሰዎች ከሚያዩት ለምጽ ነጻ ተፈወሰ፤ ቡራቡሬ የነበረው ሰውነቱ እንደሕፃን ልጅ ገላ ታደሰ፤ አዲስ ሰው ሆነ።

እንዲሁም ዛሬም የቤተክርስቲያንን አባቶችና አባታዊ ምክራቸውን፥ ትምህርታቸውን ሰምቶ እግዚአብሔር በሚያደርገው ድንቅ ተአምር ሳያንጐራጉሩ ማመን፥ ሳይጠራጠሩም እግዚአብሔር የኃይሉ መግለጫ ባደረገው ቅዱስ ጠበል በመጠመቅ አፍአዊ ከሆነ በሽታ መፈወስ ብቻ ሳይሆን መምህራን የሚነግሩንን አማናዊ ቃለ ሕይወት ሰምቶ ውሳጣዊ ከሆነና እግዚአብሔር ብቻ ከሚያየው የኃጢአት ለምጽና በሽታ መዳን
ያስፈልጋል። ትውልዱ የእግዚ
ሔርን ሥራ ማመን ሲቸግረው
ለእግዚአብሔር የሚሆን ልበ
እግዚአብሔርም ሥራውን የሚ
በት የተቀደሰ ሕይወት ሲያጣ እ
አብሔር ኃይል የሚያደርግባቸ
የድንቅ ምክንያቶች ሁሉ እየ
ባለበት ዘመን የምንገኝና ክርስቲያ
ነን የምንል የዘመኑ ሰዎችም ከ
ርቀን ይልቁንም የእግዚአብሔር
መቅደስ፥ ማደሪያዎቹ መሆናች
አምነን እግዚአብሔር በሕይ
ችን፥ በንግግራችን እንዲያ
የኃጢአት ለምጽ፥ የቂምና የበ
ለምጽ፥ የቅናትና የክፋት ለ
የሚያስቃዩቸውን ወገኖች ለማ
ምክንያት ለመሆን እንዘጋጅ።

ይህ ብቻ አይደለም እንግ
የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነ የእ
ሰውነት የዚን ያህል ተለውጦ ለሰ
ሕይወት መዳን አብነት ሆኖ ይሆ
የንዕማንን በመሰለ አፍአዊ ለም
የመጻጉዕን በመሰለ ሽባነት በዮሐ
ወንጌል ምዕራፍ ዘጠኝ እንደተ
ቀሰው ባለ የዓይን ዕውርነት ሳይ
ውሳጣዊ ለምጽ የያዛቸውንና ሕ
ታቸው ቡራቡሬ ሆኖ በእግዚአብሔ
ፊት ለመቆም የሚያሳፍራቸው
በኃጢአት በሽታ ሽባ ሆነው
መጻጕዕ ይቱ አማናዊት ቤተሳ
(ቤተክርስቲያን) የሚወስዳቸው
ተው ለዘመናት በዚህ ደዌ ኃጢአ
የሚሰቃዩትን፥ በሥጋቸው የሚ
እየመሰላቸው በአእምሮአቸው የታ
ሩትን፥ በነፍሳቸው በጨለማ ሕይወ
የሚመላለሱትን ዕውራን ልበ
በእግዚአብሔር ቃል የሚያንፃ፥ የ
ፈውስና የሚያበራ ሕይወት ያለ
ክርስቲያን ነው፥ በእርግጥ የእግዚ
ብሔር ሰው፥ እውነተኛ ክርስቲ
ሊባል የሚችለው።

የብዙዎቻችን ሕይወት (ኑሮ) ሥራችንና ንግግራችን ሰዎችን የኃጢአት ስምጽ የሚያስይዝ፣ ጤነኛውን በሽተኛ የሚያደርግ፣ ደዌ ነፍስ የሚያስይዝ፣ ልቡናው ብሩህ የሆነውን የሚያሳውርና ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሚመልስ ለሕይወት ለሚጠራ ይልቅ ከቤተ ክርስቲያን የሚያርቅ፣ ከሕይወት የሚያሸሽ በሆነና በመሳሰሉ ብቻ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ከዮርዳኖሱ ውኃ ከቤተሳይዳውና ከሰሊሆም መጠመቂያ እጅግ አንሰን እንታያለን።

እግዚአብሔር አክብሮ ማደሪያዎቹ አድርጓልና ማንነታችንን ረስተን የኛ በምንለው የአላዋቂዎች ጥበብ ከእግዚአብሔር የማዳን ኃይል እንዳንርቅ ከቸርነቱም እንዳንወጣ በሥራው ላይ ከማመጽ ይልቅ በንስሐ ራሳችንን ብናርም፣ ሕይወታችንን ብንለውጥ፣ ልቡናችንን ብናድስ መልካም መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል። ሮሜ 12፥2። ስለዚህ ካስነወረን የኃጢአት ስምጽ፣ ሽባ ካደረገን ከኃጢአት ደዌ፣ ምስጢርን ሰውሮ ማስተዋልን አጥፍቶብን በልቡናችን ዕውር ካደረገብን የትዕቢት በሽታ የሚያነጻውን የንስሐ ሕይወት ገንዘብ አድርገን በማየ ገቦው ታጥበን በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ ታትመን ዘላቂ ለሆነ ሕይወት መንግስተ ሰማያት እንድንበቃ እግዚአብሔር በቸርነቱ፣ ወላዲተ አምላክ በረድኤቷ፣ መላእክት በጥበቃ፣ ቅዱሳን በአማላጅነታቸው ከሁላችን ጋር ይሁን።

**ወይትባረክ እግዚአብሔር**

አባ ወልደ ትንሳኤ አያልነህ
ከሐመር የካቲት 1985 ከጻፉት ላይ የተወሰደ